## ቀስተ ደመና ሬድዮ ትችት 26.10.01

## ጸረ ሽብሩ ትግልና መናጢ ድህነት

ባለፈው አጭር ደብዳቤየ በኒውዮርክና ዋሽንግተን ሽብር ፈጣሪዎች ባደረሱት አሰ
ቃቂ አደጋ ሳቢያ ያአሜሪካን መንግስት ሽብር ፈጣሪዎቹን ይዞ ፍርድ ለማቅረብ በመውሰ
ድ ላይ ስላለው የማጥቃት ርምጃና ባጠቃላይም ሽብር ፈጠራን ከምድር ገጽ ለማጥፋት በ
አለም አቀፍ ደረጃ ስለተጀመረው ሰፊ እንቅስቃሴ ጠቅሸ ይህ አለም አቀፍ ትግል ስላስነሳ
ው ክርክር አውስቻለሁ። የዚህ ክርክር ዋና ዋና ነጥቦች ሁለት ሲሆኑ የመጀመሪያው ዛሬ
የማተኩርበት ጥያቄ ሽብር ፈጠራ አሁን ካለበት ለአሜሪካን ብቻ ሳይሆን ለመላው ያለም
ህዝቦች ሊተርፍ የሚችልበት ደረጃ ያደረሱትና በእርግጥም በመጭው ጊዜ እስካሁን ካየነ
ው በሰፋና በከፋ ሁኔታ ሊቀጥል የሚያስችሉት የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ ምክን
ያቶች ምንድን ናቸው በሚለው ጥያቄ ዙሪያ የተከሰተው ክርክር ነው። አንዳንዶች እንደ
ሚቃጣቸው እነዚህን ጥያቄዎች ፊት ለፊት ተጋፍጦ ተገቢ መልስ ከመስጠት ይልቅ ስለ ሽ
ብር ፈጣሪዎች ፋናቲክነት፣ ስለ አክራሪነታቸው፣ አንዳንዴም ያእምሮ መታወክ ችግር በ
መጥቀስ መገላገል የሚቻል አይመስለኝም። በአለፈው ደብዳቤየ እንዳልኩት ጥያቄው በእ
ርግጥም አእምሮዋቸው ታውኩዋልሊባል ስለሚችሉ ጥቂት ግለሰቦች ብቻ የሚመለከት ጥ
ያቄ አይደለም። ጥያቄው የተወሰኑ ባንዳንድ አገሮች እንዲያውም የማይናቁ ሊባሉ የሚች
ሉ የህዝብና የህብረተሰብ ክፍሎች ለምን ይደግፉዋቸዋል የሚለው ጥያቄ ነው። ለዚህ ጥ
ያቄ ደግሞ ይህ ሽብር ፈጣሪዎችን ደግፎ በገፍ የሚንቀሳቀስህዝብ ሁሉ አብዱዋል ካልተባ
ለ በስተቀር መልስ ሊሰጥ የሚቻለው ከዚህ እንቅስቃሴ ጀርባ ያሉትን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲ
ካና የማህበራዊ ችግሮች በመመርመር ብቻ ነው።

ዛሬ በዚህ ጥያቄ ላይ አጠቃላይ ስምምነት ያለ ይመስላል። በመስከረም አንዱ ጥቃ
ት ማግስት ጆርጅ ደብልዩ ቡሽ ራሳቸው ለአለምም ላሜሪካንም ህዝብ ባደረጉት ንግግር በ
ዚህ በሃያ አንደኛው ክፍለዘመን መግቢያ ላይ የተጀመረው አዲስ አይነት ጦርነት መሆኑን
ተንብየው በተከታታይ ቀናት ከዋሽንግተንም ሆነ ከለንደን እንደዚሁም ከሌሎች የአውሮፓ
ከተሞች የተሰጡት መግለጫዎች ከተከፈተው «ያጠቃላይ ሽብር» ወይም ግሎባል ቴረሪዝ
ም ዘመቻ አንጻር ተገቢ የሚሆነው አጸፋ ወታደራዊ ብቻ ሳይሆን ዲፕሎማሲያዊ፣ ፖለቲ
ካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የሆነ አጠቃላይ አጸፋ መሆን ይገባዋል የሚል አስተሳሰብ
እናያለን። ካንድ ወር በፊት በዚህ ጉዳይ ቀስተ ደመና ሬድዮ ባስደመጠው አንድ ዘገባ የ
አሜሪካንና የታላቁዋ ብሪታንያ መንግስት ባለስልጣናት አጸደቁት የተባለው አንድ «ኦፐሬሽ
ን ኖብል ኢግል» በሚል የተሰየመ ሰነድ እነዚህኑ ነጥቦች በማስመር አጠቃላዩ ጸረ ሽብር
ዘመቻ ቢያንስ ቢያንስ ከአምስት እስከ አስር አመታት እንደሚወስድና ትግሉ ከድረግስ ነጋ
ዴዎች፣ ከሌላ የተደራጀ ወንጀል (ኦርጋናይዝድ ክረይም) አራማጆች ጋርና ባለም አቀፍ ደ
ረጃ ድህነትን ለመቅረፍ የሚደረግ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ትግል እንደሚሆን በግልጽ ያስ
ቀመጠው ጉዳይ ነው።

ለሽብርተኞች በር ለመዝጋትና ህዝባዊም ሆነ ማህበራዊ መሰረት ለማሳጣት ከተፈለ
ገ በእርግጥም በአለም አቀፍ ደረጃ እየሰፋና እየከፋ በመሄድ ላይ ያለውን በመቶ ሚልዮን
የሚቆጠሩ ህዝቦችን ከሰውነት ውጭ እያስወጣ ያለውን የተዛባ ሁኔታ መታገል አስፈላጊነ
ት ዛሬ ባለም ደረጃ «ልኡሉም ለማኙም» እየተገነዘበው የሄደ ሃቅ ነው። ይህ ደግሞ አዲ
ስ ነገር አይደለም። ቀዝቃዛ ጦርነት የተባለው ከተደመደመ ወዲህ እየተተከለ በአለው አ
ዲስ አለም አቀፋዊ የግሎባላይዜሽን ስርአት በየግለሰብ አገሮችም ሆነ በአለም አቀፍ ደረ
ጃ ከፍተኛ የሆነና እየሰፋ የሄደ የገቢ አለመመጣጠን እየተከሰተ ነው። በተለይ ከአለማች
ን ደቡብ ክፍል ህዝቦች አብዛኞቹ ከዛሬ አስር አመት ዛሬ ይበልጥ ጎስቁዋላ መሆናቸውን
ና ለቅጥ ያጣ ድህነት መዳረጋቸውን ለመረዳት ሌላው ቀርቶ የተባበሩት መንግስታት ድር
ጅት የልማት ፕሮግራም (የዩኤንዲፒ) ኤክስፐርቶች በያመቱ የሚያወጡዋቸውን ዘገባዎች

መመልከት ብቻ ይበቃል። አካባቢያችንን ብንመለከት ደግሞ በኢትዮጵያም ሆነ በኤርትራ ና፣ በሱማሊያ ከህዝቡ ስንት በመቶው ነው ከዛሬ አስር አመት ዛሬ የተሻለ ኑሮ የሚኖረ ው? ይህ ማለት ግን ለምሳሌ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚው እድገት አላደረገም ማለት አይደለም ። አድርጉዋል። የሃገር አጠቃላይ እድገት ከህዝብ ኑሮ መሻሻል ጋር ግን ምንም ግንኙነት የለውም። እናቶ መለስ ዜናዊ በዚህ አመት ኢኮኖሚያችን ይህንን ያህል አደገ ሲሉ የኢት ዮጵያ ህዝብ «በህልሜ ነው በውኔ ወይስ በቴሌቪዥን» አይልም። በጥቂቶች እጅ የሃብት መከበትና መንደላቀቅ ቅጥ ባጣ ሁኔታ ሲስፋፋ በየእለቱ ይታዘባል። በዚህም የተነሳ ህዝባ ችን የሚለው «አወን ኢኮኖሚው አድጉዋል ግን ለኔ ምንም የተረፈኝ ነገር የለም እንዲያ ውም ችግሩ ማጣቱ መራቆቱ ጠንቶብኛል» ነው። ባጭሩ ለማስቀመጥ በአዲሱ አለም አቀ ፋዊ ስርአት ድህነትና ማጣት ተስፋፍተዋል የሚለው አስተሳሰብ ስር እየሰደደ መጥቱዋል።

ሁሉም ሌላው ቢቀር ለአለም ሰላም ሲባል ድህነትን ማስወገድ ያስፈልጋል ባይ ሆን ዋል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ባስራ አምስት አመታት ውስጥ ከመናጢ ድህነት እ ርከን በታች (ማለትም በቀን በነፍስ ወከፍ ከአንድ የአሜሪካን ዶላር ወይም ስምንት የኢት ዮጵያ ብር በታች ገቢ ያላቸውን ሰዎች) ቁጥር በግማሽ ለመቀነስ ብሎ ያወጣው ፕሮግራ ም ገና ከመሬት ሳይነሳ ሲንደፋደፍ ከቆየ በሁዋላ ከሁለት ወራት በፊት የፕሮግራሙ ሃላፊ በሰጡት መግለጫ «ነገሩ እንደታሰበው ቀላል አይሆንም» ሲሉ ተደምጠዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም የሚሉት ፈሊጥ መጥቱዋል። በአለፉት አስርት አመታት «ልማትን ለማፋጠን» በሚል ሰበብ ባለም አቀፍ የፋይናንስ ድ ርጅቶች ተቀይሶ በድሆች አገሮች ላይ ተጭኖ ሲያተራምሳቸው የነበረው «የመዋቅር ማስ ተካከያ ፕሮግራም» የተባለው አካሄድ ውድቅ መሆኑ ከተጋለጠ በሁዋላ አሁን ደግሞ መ ከረኞቹን የደቡብ አገሮች ህዝቦች ባገር በቀል ሃይሎች ትብብር እንደላቦራቶሪ አይጦች ሌላ ፕሮግራም እየተፈተሸባቸው ነው።

የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ፕሮግራም የሚለው ሃሳብ በመስከረም 1992 እ.ም. በአለ ም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አመታዊ ጉባኤ ከጸደቀና በጀት ከተያዘለት ወዲህ በዚህ ፕሮግ ራም ሊሳተፉ ይችላሉ ከሚባሉት ሰባ ሰባት በመደህያት ላይ ያሉ አገሮች አብዛኞቹ የአለ ም የገንዘብ ድርጅትና ሌሎች አለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት አውጥተው የሰጡዋቸው ን ፎረም እየሞሉ የገንዘብ እርዳታ ማመልከቻ ማስገባት ጀምረዋል። ከአመት ተኩል ጀም ሮ ድሃ ተብየ አገሮች መንግስታት የተያያዙት አዲስ ፈሊጥ ይኸ ሆኖ እስካሁን ድረስ 45 ያህል አገሮች «የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ» የተባለውን ማመልከቻ አስገብተዋል።

ሰሞኑን የወያኔ መንግስት የህንኑ «የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ» በሚል ያሰናዳ ውን አንድ ባለ ሰላሳ ስድስት ገጽ ጽሁፍ ለአለም ባንክ፣ ላለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና ለሌሎች የፋይናንስ ተቋዋሞች ማቅረቡ ይፋ ሆንዋል። የዚህ የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም መ ሰረታዊ እቅድ «የእርሻ ልማትን መሰረት ያደረገ የኢንዱስትሪ እድገት» ወይም «አግሪከል ቸር ዲቨለፐሜንት ሌድ የንደስትርያላይዜሽን» (አድሊ) የተባለው ስትራቴጂ ሲሆን ከመጀ መሪያ እስከመጨረሻ አለም አቀፍ የፋይናንስ ድርጅቶች በአለም ላይ ለመጫን የሚፈልጉ ትን የለየለት የሊብራል ኢኮኖሚ መሰረታዊ ፍልስፍናዎች የተከተለ ፕሮግራም ነው። እንደ ቀደመው «የመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም» ይኸም ውድቅ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለ ም።

ይህም ሆኖ ይህ የወያኔ ፕሮግራም በሌሎች መንግስታት እስካሁን እንደቀረቡት አር ባ አምስት ያህል የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነዶች (የሁሉም ስም አንድ ነው) በአለም ባን ክ ባለስልጣናት ተደንቁዋል። ባለፈው ሳምንት የዚህ ተቋዋም ዋና ኢኮኖሚስት ሚስተር ኒ ኮላስ ስቴርን የቀደሙትን ሰነዶች እንዳሞገሱት ሁሉ ይህንንም የወያኔን ሰነድ «ሁለ ገብ፣ ዳይናሚክእና የሚደነቅ» በማለት አሞካሸተውታል። በዛሬይቱ አለም ከሰፈነው አንድ ወጥ አስተሳሰብ ለየት ያለ እይታ ያላቸው ኢትዮጵያውያን የኢኮኖሚ ምሁራን ዝርዝር ሁኔታው ን ተንትነው ለኢትዮጵያም ህዝብ ሆነ ለታጋዮች እንደሚያብራሩት ተስፋ አደርጋለሁ። እ ዚህ ላይ ግን አንድ መሰረታዊ ነጥብ አንስቸ ስለዚህ «የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ» ሃሳብ ለ ጊዜው ልደምድም።

የአለም ባንክ ይህንን ፕሮግራም አድንቆ ከመቀበል አልፎ በተግባር እንዲተረጎም ለ
መርዳት በሶስት አመት ውስጥ ለወያኔ መንግስት የሚሰጥ የመቶ አስር ሚልዮን ዶላር ብድ
ር ባለፈው የካቲት መጀመሪያ ላይ ፈቅዶዋል። ካለፈው የመዋቅር ማስተካከያ ውድቀት
ትምህርት ተቀስሞ የዛሬ ሁለት አመት ይህ የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም ሃሳብ ሲጸድቅ መሰረ
ታዊ ነው ተብሎ ቀርቦ የነበረው ሃሳብ እንዲህ አይነቱ ስትራቴጂ በእርግጥ እንዲሰራ ከተ
ፈለገ አንዳደፉ ህብረተሰቡን በሙሉ በሚያሳትፍ መልክ እንጂ በጥቂት ኤክስፐርቶች ተነ
ድፎ ለህዝቦች ያውላችሁ ተብሎ እንዳይወረወር ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ በግል
ጽ ተነግሮ ነበር። የአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ጉባኤ ይህንን የህብረተሰብ ተሳትፎ ሃሳ
ብ እንደሚከተለው አስቀምጦት ነበር፣

« አለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ከአለም ባንክ ጋር በመተባበር ተበዳሪ አገሮች ድ
ህነትን ለመቀነስ ስትራቴጂ ሰነዶች እያወጡ መንቀሳቀሳቸውን ይደግፋል። እነዚህ ሰነዶች
ም በሲቪል ማህበረተሰቡ አባላትና እንደዚሁም በድሆችና በሌሎች የልማት ጉዳይ በሚያገ
ባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ መነደፍ ይኖርባቸዋል» በሚል አስቀምጦት ነበር።

የሃገራችን የሲቪል ማህበረሰብ አባላት፣ የሃገራችን ድሆች፣ በልማት ጉዳይ ያገባና
ል የሚሉ ነጋዴዎች፣ ኢንቬስተሮች፣ ምሁራን ወዘተ ይህንን ለአለም የገንዘብ ድርጅት ባለ
ፈው አመት በህዳር ወር የቀረበ ሰነድ መቼና በየትኛው መድረክ ነው የተወያዩበት? መል
ሱ ግልጽ ነው። መቼም የትም አልተወያዩበትም። ለምን? በሃገራችን አለ የሚባለው ዴሞክ
ራሲ ለማንም ለማንም ሳይሆን በስድ ገበያው ኢኮኖሚ ግርግር ተጠቃሚ ለሆኑት ጥቂቶች
ብቻ የሚሰራ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚባለው አፋኝ ዴሞክራሲ ተብየ ነገር ነው። ለአንዳ
ንዶች እንግዳ ነገር ቢመስልም በመተከል ላይ ያለው ግፈኛና ህዝባችንን ለከፋ ድህነት እየ
ዳረገ በመሄድ ላይ ባለው ሊበራል የገበያ ኢኮኖሚና በአብዮታዊ ዴሞክራሲ መሃከል ምን
ም አለመጣጣም ወይም ቅራኔ የለም። በሚተከለው ግፈኛ ስርአት ተንገፍግፎ ህዝባችን እን
ዳይንቀሳቀስ ከተፈለገ አፋኝ የፖለቲካ ስርአት የግድ ነው። ዛሬ ባለው የሃገራችንም ሆነ የ
አለም አቀፍ ሁኔታ ስድ ገበያና አብዮታዊ ዴሞክራሲ እጅና ጉዋንት ሆነው የሚራመዱ ክ
ስተቶች ናቸው።

ወደ አርእስቱ ልመለስና ዛሬ በአለም አቀፍ ደረጃ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት ቅጥ ያ
ጣ ድህነትን መቅረፍ ያስፈልጋል ቢባልም ይህ የድህነት መቅረፊያ ዘዴ ምንድን ነው በሚ
ለው ላይ ስምምነት የለም። አሁን በተያዘው የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ተብየ ነገር መቀጠ
ል ማለት ድህነትን ማስፋፋትና ማክፋት ስለሆነ የትም አያደርስም። ሂደቱ ሁሉ ውጤታማ
እንዲሆን ከተፈለገ ህዝቦች በየሀገሮቻቸው እንደ ልማት ደረጃቸው፣ እንደባህላዊ ቅርሶቻ
ቸው፣ እንደ ህልማቸው፣ እንደፍላጎታቸውና ጉጉታቸው የራሳቸውን እድገት አቅጣጫና ፍ
ጥነት ለመወሰን የሚችሉበት ዴሞክራሲያዊ ስርአት መገንባት ይኖርባቸዋል። ከዚህ ውጭ
ግን በመላ አለም አንድ አይነት ኢኮኖሚ፣ አንድ ወጥ ስርአት፣ አንድ ወጥ የእድገት ጎዳ
ናና አቅጣጫ ለመጫን የሚደረገው ጥረት ሁሉ ድህነትንም አይቀርፍም፣ ሽብርተኞችን የ
ሚፈለፍሉትን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ምክንያቶች አያጠፋቸውም። እነዚህ እ
ስካልተነኩ ድረስ ደግሞ ሽብርን ለመዋጋት የሚቀረው ወታደራዊ መፍትሄ ብቻ ይሆናል።
ችግሩ ይህ ብቻውን መፍትሄ እንደማይሆን ሌላው ቀርቶ እነፕሬዜዳንት ጆርጅ ደብልዩ ቡ
ሽ እንኳዋን የተገነዘቡት ሃቅ መሆኑ ነው።